# Barnebøker for Norge

barneboker.no

## ሲምበግዊሬ

Skrevet av: Rukia Nantale
Illustret av: Benjamin Mitchley
Oversatt av: Mezemir Girma

Denne fortellingen kommer fra African Storybook (africanstorybook.org) og er videreformidlet av Barnebøker for Norge (barneboker.no), som tilbyr barnebøker på mange språk som snakkes i Norge.

Dette verket er lisensiert under en Creative Commons
Navngivelse 3.0 Internasjonal Lisens.
https://creativecommons.org/licenses/by/3.0/deed.no

# ሲምበግዊሬ

Rukia Nantale
Benjamin Mitchley
Mezemir Girma
amharisk
nivå 5

(uten bilder)

ሲምበግዊሬ እናቷ ስትሞት ብስጭት ተሰማት። የሲምበግዊሬ አባት ለልጁ እንክብካቤ ለማድረግ የተቻለውን አደረገ። ቀስ በቀስ የሲምበግዊሬ እናት በሌለችበት ደስተኝነትን መልሰው እንዴት እንደሚያገኙ አወቁበት። በየዕለቱ ጠዋት ቁጭ ብለው ስለመጪው ቀን ይነጋራሉ። በየምሽቱም ራት አብረው ይሰራሉ። ሳህኖቹን ካጠቡ በኋላ የሲምበግዊሬ አባት የቤት ስራዋን በመስራት ያግዛታል።

አንድ ቀን የሲምበግዊሬ አባት ከወትሮው አምሽቶ መጣ። ‹‹የት ነሽ ልጄ?›› ሲል ተጠራ። ሲምበግዊሬም ወደ አባቷ ሮጠች። አባቷ የአንዲት ሴትዮ እጅ መያዙን ስታይ ቀጥ ብላ ቆመች። ‹‹ልጄ፣ አንዲት ልዩ የሆነች ሴትዮ እንድትተዋወቂ እፈልጋለሁ። ይህች አኒታነች›› አለ ፈገግታ እያሳየ።

<<እንዴት ነሽ ሲምበግዊሬ? አባትሽ ስላንቺ ብዙ ነገር ነግሮኛል>> አለቻት አኒታ። ይሁን እንጂ አኒታ ፈገግታ አላሳየችም፤ ወይም የሲምበግዊሬን እጅ አልጨበጠችም። የሲምበግዊሬ አባት ደስተኝት ተሰማው። ሦስቱ አብረው ስለሚኖሩበት ሁኔታና ህይወታቸው እንዴት ጥሩ እንደሚሆን አወራ። <<ልጄ፣ አኒታን እንደ እናት እንደምታያት ተስፋ አደርጋለሁ>> አላት።



በቀጣዩ ሳምንት አኒታ ሲምበግዊሬን ከአክስቷና ከልጆቿ ጋር በቤቷ ምሳ ጋበዘቻቸው። ምን ዓይነት ግሩም ድግስ ነው! አኒታ ሲምበግዊሬ የምትወዳቸውን ምግቦች ሁሉ አሰናዳች እና ሁሉም ሰው እስከሚጠግብ ድረስ በላ። ከዚያም አዋቂዎቹ ሲያወሩ ልጆቹም ተጫወቱ። ሲምበግዊሬም ደስተኝነትና ጀግንነት ተሰማት። በቅርቡ፣ በጣም በቅርቡ፣ ወደቤቷ እንደምትመለስና ከእናቷና ከእንጀራ እናቷ ጋር እንደምትኖር ወሰነች።

አባቷ በየቀኑ ይጠይቃት ጀመር። አንድ ቀንም ከኢኒታ ጋር መጣ። ኢኒታም ሲምበግዊሬን ለመጨበጥ እጇን ዘረጋች። ‹‹ልጄ አዝናለሁ፤ ተሳስቻለሁ›› በማለትም አለቀሰችባት። ‹‹እንደገና አንድ ዕድል ትሰጪኛለሽ?›› ሲምበግዊሬም አባቷንና የተጨነቀ ፊቱን አየች። ከዚያም በኋላ ቀስ ብላ ወደፊት ጠጋ አለችና ኢኒታን አቀፈቻት።



የሲምበግዊሬ ህይወት ተቀየረ። ጠዋት ጠዋት ከአባቷ ጋር ለመቀመጥ ጊዜ እያጣች መጣች። ኢኒታ በርካታ የቤት ውስጥ ስራ ስለሰጠቻት ማታ ማታ የቤት ስራዋን ለመስራት በጣም ይደክማት ጀምር። ከእራት በኋላ ቀጥታ ወደ መኝታዋ መሄድ ልማዷ እየሆነ መጣ። የሚያጽናናት ብቸኛው ነገር እናቷ የሰጠቻት በቀለም ያበደ ብርድ ልብስ ነበር። የሲምበግዊሬ አባት የልጁን መከፋት ልብ ያለው አይመስልም።

ከጥቂት ወራት በኋላ የሲምበግዊሬ አባት ለተወሰነ ጊዜ ራቅ ብሎ እንደሚሄድ ነገራቸው። ‹‹ለስራ ጉዳይ መሄድ አለብኝ›› አላቸው። ‹‹እርስ በእርሳችሁ እንደምትደጋገፉ ግን እተማመናለሁ።›› የሲምበግዊሬ ፊት ቅይርይር አለ፤ አባቷ ግን ይህን ልብ አላለም። አኒታ ምንም ቃል አልወጣትም። እርሷም ደስተኝነት አልተሰማትም ነበር።



ሲምበግዊሬ ከአክስቷ ልጆች ጋር እየተጫወተች ሳለች አባቷን ከሩቅ አየችው። ይናደድብኛል ብላ ፈራች። ስለሆነም ለመደበቅ ወደቤቱ በኩል ሮጠች። አበቷ ግን ወደሷ ሮጦ ‹‹ሲምበግዊሬ ጥሩ እናት አግኝተሻል - የምትረዳሽና የምትወድሽ። እኮራብሻለሁ፤ እወድሻለሁ›› አላት። ሲምበግዊሬ ከአክስቷ ጋር እስከፈለገችበት ጊዜ ደረስ እንድትቆይም ተስማሙ።

የሲምበግዊሬ አባት ወደቤቱ ሲመለስ ቤቱን ባዶ አገኘው። ‹‹ምን ተከሰተ አኒታዬ?›› አላት ክብድ እያለው። ሲምበግዊሬ መጥፋቷን ነገረችው። ‹‹እንድታከብረኝ ስፈልግ ነበር›› አለች። ‹‹ምናልባት ከረር አድርጌባት ሊሆን ይችላል።›› የሲምበግዊሬ አባት ቤቱን ጥሎ ወደ ምንጩ በኩል ሄደ። ሲምበግዊሬን አይታት እንደሆነ ለመጠየቅም ወደ እህቱ መንደር ዘለቀ።



ለሲምበግዊሬ ነገሩ ሁሉ እየከፋ ሄደ። ስራዎቿን ካልጨረሰች፣ ካማረረች፣ አኒታ ትመታት ጀመር። በእራት ሰዓትም ሴትዮዋ ብዙውን ምግብ ስለምትበላው ለሲምበግዊሬ የሚደርሳት ፍርፋሪ ነበር። በየምሽቱ ሲምበግዊሬ ወደ እንቅልፏ የምትሄደው እያለቀሰች ነበር፤ የእናቷን ብርድልብስ እያቀፈች ትተኛለች።

አንድ ቀን ጠዋት ሲምበግዊሬ ተኝታ አረፈደች። ‹‹አንቺ ሰነፍ!›› አኒታ አምባረቀችባት። ሲምበግዊሬን ጎተተቻት። ያን ውድ ብርድልብስ ምስማር ያዘውና ከሁለት ተቀደደ።



የሲምበግዊሬ አክስት ልጅቱን ወደቤቷ ወሰደቻት። ለሲምበግዊሬም ትኩስ ምግብ ሰጠቻት፤ የእናቷን ብርድልብስም አለበሰቻት። በዚያ ምሽት ሲምበግዊሬ ወደ መኝታዋ ስትሄድ አለቀሰቸ። እንባዋ ግን የእፎይታ እንባ ነበር። አክስቷ እንደምትንከባከባት አውቃለች።

ይህች ሴት ቀና ብላ ዛፉን አየች። ልጅቱንና የብርድልብሱን ቁራጭ ስታይ ‹‹ሲምበግዊሬ፣ የወንድሜ ልጅ!›› ስትል ጮኸች። ሌሎቹም ሴቶች ማጠባቸውን አቁመው ሲምበግዊሬን ከዛፉ እንድትወርድ አገዟት። አክስቷ ትንሿን ልጅ አቅፋ ታጽናናት ጀመር።



ሲምበግዊሬ በጣም ተበሳጨች። ከቤት ለመጥፋት ወሰነች። የእናቷን ብርድልብስ ቁራጮች ይዛ፣ ጥቂት ስንቅ ቋጠራ ቤቱን ለቃ ሄደች። አባቷ የሄደበትን መንገድም ይዛ ጉዞዋን ጀመረች።

ሲመሸባት ከአንድ ምንጭ አጠገብ ካለ ትልቅ ዛፍ ላይ ወጥታ ከቅርንጫፎቹ ላይ መኝታዋን አዘጋጀች። እየተኛችም ሳለች ‹‹እናቴ፣ እናቴ፣ እናቴ፣ ተውሽኝ። ተውሽኝና አልመለስ አልሽ። አባቴ አሁን ለኔ ማሰቡን ተቷል። እናቴ፣ መቼ ነው የምትመጭው? ተውሽኝ እኮ›› በማለት አዜመች።



በቀጣዩ ማለዳ ሲምበግዊሬ ዘፈኑን ደግማ ዘፈነችው። ሴቶች ልብሳቸውን ለማጠብ ወደ ምንጩ ሲመጡ ከትልቁ ዛፍ የሚመጣውን የመከፋት ዘፈን ይሰሙ ጀመር። ንፋሱ ቅጠሉን እያማታ የሚፈጥረው ድምጽ መስሏቸው ስራቸውን ቀጠሉ። ከሴቶቹ አንዷ ግን ዘፈኑን በጣም በጥንቃቄ አደመጠችው።